በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ... - ክፍል 3


**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**<u>E-mail:</u>** kesisolomon4@gmail.com


***<u>ቦታ፡-</u>*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

የካቲት ፳፰ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ... - ክፍል 3

## የተወደደ - ምርጥ ጊዜ

- የሰው ልጅ በምድር በሚኖረው ዕድሜው ይጠቀምበት ዘንድ የተሰጠው የሚደነቅ ስጦታ ጊዜ ነው፡፡ ጊዜ ያለፈውን ጊዜ ወይም ደቂቃ የሚመልስ ማካካሻ አይደለም - ያለፈ ጊዜ አይመለስምና!
- ቢረዝምም ቢያጥርም በምድር ያለን ዕድሜ በሚቆጠሩ ዓመታት የተገደበ ነው፡፡ ስለጊዜ ያለን ግንዛቤ መስተካከሉም ሆነ ጊዜን እንዴት ባግባቡ እንደምንጠቀምበትም ማወቅ አስፈላጊ የሆነው ለዚህ ነው፡፡
- ‹‹እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ፤ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ፡፡›› *ኤፌ 5፡15-16፡፡*
- አንዳንድ ሰዎች ጊዜን ‹‹ሲያጠፉ›› ተወዳዳሪ አይገኝላቸውም፡፡ ሌሎች ደግሞ የጊዜ ትልቁ ዋጋው ‹‹ገንዘብ›› ነው ብለው ያምናሉ፤ እነዚህም እያንዳንዱ የሚያጠፉት ደቂቃ ተጨማሪ ገንዘብ እንደሚያመጣላቸው ወይም እንደሚያስገኝላቸው ያምናሉ፡፡
- እንዲሁም ከዚህ ውጪ የሆኑት ሌሎች ደግሞ እያንዳንዷ ደቂቃ በሕይወታቸው ውስጥ ለውጥ ለማምጣት ካልዋለች ፍጹም እርካታን አያገኙም፡፡ ሌሎችም የሕይወታቸውን እያንዳንዱን የሕይወታቸውን ደቂቃ ለአገልግሎት ያውሉታል፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 3

## የተወደደ - ምርጥ ጊዜ

- ሠርተን ለሕይወታችን የሚያስፈልገንን ማግኘታችን ስሕተት የለውም፣ ለራሳችን እርካታን የምናገኝበትን ሥራ መሥራታችንም በጣም መልካም ነው፣ አገልግሎት መስጠትም ታላቅ በረከት ነው፣ ስኬታማነትም ይደነቃል…
- ቁልፉ ጥያቄ ግን እነዚህን የመሰሉ ተግባራት ስናከናውን - ጊዜያችንንም ስንጠቀምበት እግዚአብሔር በሕይወታችን ያለውን እቅድ ማሳካታችን ነው፡፡ እርሱም እግዚአብሔርንና በዙሪያችን ያሉትን ሁሉ በፍጹም ኃይላችን፣አሳባችን፣ ነፍሳችንና ልባችን እንወድ ዘንድ አይደለምን? ‹‹እርሱም አለው፡- ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም ኃይልህም በፍጹም አሳብህም ውደድ፥ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው፡፡›› *ሉቃ 10:27፡፡*
- ማድረግ የሚገቡንን ታላላቅ ሥራዎች ሁሉ ስናደርግ ወይም ስንሠራ ‹‹የተወደደ መልካም ወይም ምርጥ ጊዜን›› ከትዳር አጋራችንና ቤተሰባችን ጋር እንጠቀማለን?!!!
- በጊዜ መርሐ ግብራችን የትዳር አጋራችንና ቤተሰቦቻችን በቅደም ተከተሎቹ የመጨረሻ መሥመር ላይ መቀመጣቸው አሳፋሪ ነው፡፡

# <u>የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 3</u>

## የተወደደ - ምርጥ ጊዜ

- *ቀኑን ሙሉ ሥራ ላይ ውለን የትዳር አጋራችን የገጠማትን አስቸጋሪ ጉዳይና ልጆቻችን ሊሻገሩት ባልቻሉት የእኛን እርዳታ የሚፈልገው ችግር ላይ መሳተፋችን ወይም ለመፍታት የሚያስችለንን ውይይት አለማድረጋችን እንደተጠበቀ ሆኖ ምንም ለመናገርም ሆነ አንዲት ቃል ለመስማት እንዳንችል ሆነን ፍጹም ተዳክመን ወደቤት መመለሳችን አሳዛኝ ነው፡፡*
- በዚህ ጊዜ ተገቢ የሆነ ‹‹የምንሰማበት ጆሮ›› ለትዳር አጋራችን ወይም ልጆቻችን አለመስጠታችን ‹‹ይህን ጆሮ›› ሊሰጣቸው ወደሚችል ሰው እንዲመለከቱ እንደሚያደርጋቸው የተረዳን አይመስልም፡፡
- *ሕይወት ፈታኝ ሆና ለቤተሰቦቻችን ማሟላት የሚገቡን ነገሮችና ኃላፊነታችን እየከበደ መምጣቱ የሚታወቅ እውነታ ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ፍላጎት ለማሟላት ረጅም ሰዓታት ወይም ሁለት ሥራዎች የመሥራት ግዴታ ይወድቅባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በትዳር አጋራችንና ልጆቻችን ቁሳዊ ወይም ስሜታዊና ሥነ ልቦናዊ ፍላጎት መካከል ተገቢውን ሚዛን አስቀምጠን መንቀሳቀስ እንደሚጠበቅብን መዘንጋት አይገባም፡፡*
- እያንዳንዳችን መሥራታችን እንደተጠበቀ ሆኖ ከትዳር አጋራችንና ቤተሰባችን ጋር ‹‹የተወደደ ጊዜን›› ማሳለፍ አስፈላጊ ነው፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 3

## የተወደደ - ምርጥ ጊዜ

- በርካታ ባለትዳሮች ጥቂት ሰዓታትን በቤታቸው ማሳለፍ ከቻሉ ሁሉን የሸፈኑና ያሟሉ ይመስላቸዋል፡፡ በቤት ቆይታችን ቲቪ ስንመለከት፣ በኮምፒዩተራችን ያሉ ጌሞችን ስንጫወት፣ ወይም ቻት ስናደርግ፣ እንግዳ ስንቀበል ካሳለፍን ይህ ጊዜ ‹‹የተመረጠ - የተወደደ ጊዜ›› አይደለም ማለት ነው፡፡
- ‹‹የተመረጠ - የተወደደ ጊዜ›› ማለት በተጋቢዎችና በቤተሰቡ መካከል ያለውን ግኑኝነት የሚያጠነክርና ጥልቅ የሚያደርገው ማንኛውም እንቅስቃሴ የሚደረግበት ጊዜ ነው፡፡
- ይህ ‹‹የተመረጠ - የተወደደ ጊዜ›› የመነጋገሪያ፣ የመምከሪያ፣ ነገሮችን የምንጋራበት፣ የምንደማመጥበት፣ የምንተዛዘንበት፣ ሐዘንና ደስታችንን የምንካፈልበት… የምናወራበት፣ የምንጫወትበት፣ የምንስቅበት፣ … ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግኑኝነት ስላላቸው በጎ ልምድ የምንነጋገርበት - ልምዳቸውን የምንካፈልበት፣ መጽሐፍ ቅዱስን አብረን የምናነብበትና አብረንም የምንጸልይበት … አንዳችንን ባሳዘነ ጉዳይ ላይ የምንማከርበት… አንዱ ሌላው የገጠመውን አስቸጋሪ ሰው ወይም ነገር አስመልክቶ የሌላውን ምክር የሚጠይቅበት ጊዜ ነው፡፡ ‹‹የተመረጠ - የተወደደ ጊዜ›› የቤተሰብ ታላቅ ምርጥ ጊዜ ነው፡፡
- ‹‹የተመረጠ - የተወደደ ጊዜ›› የተወደደ ሁኔታን በቤት ውስጥ በመፍጠር የቤተሰቡ አባላት በቤታቸው የሚያደርጉት ቆይታ ረዘም ያለ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ ሁሉም ፈጥነው ከሐዘናቸው፣ ሐሳባቸው፣ ስኬታቸው፣ ፈተናዎቻቸው ወይም የቀን ውሎ ታሪካቸው ጋር ወደቤታቸው እንዲሮጡ ያደርጋቸዋል፡፡

# <u>የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 3</u>

## ኃላፊነት

- ኃላፊነት አንድ ሰው በብቃት ሊያከናውነው ወይም ሊወጣው የሚገባው ሥራ ወይም ግዴታ ነው፡፡
- ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለበት የሚሰማው ሰው የየዕለት ሥራውን ባማረ መልክ ለማከናወን ይጣጣራል፡፡ ‹‹አንተ ታካች፥ ወደ ገብረ ጕንዳን ሂድ፥ መንገድዋንም ተመልክተህ ጠቢብ ሁን፡፡አለቃና አዛዥ ገዢም ሳይኖራትመብልዋን በበጋ ታሰናዳለች፥ መኖዋንም በመከር ትሰበስባለች፡፡አንተ ታካች፥ እስከ መቼ ትተኛለህ? ከእንቅልፍህስ መቼ ትነሣለህ?ጥቂት ትተኛለህ፥ ጥቂት ታንቀላፋለህ፥ ትተኛም ዘንድ ጥቂት እጅህን ታጥፋለህእንግዲህ ድህነትህ እንደ ወንበዴ፥ ችጋርህም ሰይፍ እንደ ታጠቀ ሰው ይመጣብሃል፡፡›› <u>*ምሳ 6፡6-11፡፡*</u>
- የትዳር አጋሮች ኃላፊነታቸውን የመወጣት ስሜትን ለትዳራቸው ስኬታማነት እንደ ከፍተኛ ቅድመ ሁኔታ አድርገው መመልከታቸው እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡
- አንዳንድ ጊዜ ይህ ኃላፊነት የወንድ ብቻ እንደሆነ መታሰቡ ስህተት ነው፡፡ ሴቶችም እንደ ሚስትና እንደ እናት ሆነው ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ይጠበቅባቸዋልና፡፡
- ኃላፊነት የማይሰማው/ት ሰው/ሴት ለትዳር አጋር/ርዋ ከፍተኛ ችግርና ጭንቀት የሚያ/ምታስከትል ታላቅ ሕመም ነው/ናት፡፡
- ኃላፊነት የሚሰማው ሰው ለሌላው ደስታና እርካታ ከፍተኛ ጥንቃቄና ክብካቤ ያደርጋል፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 3

## ኃላፊነት

- የመፈጠራችንን፣ የመዳናችንንና ዘላለማዊ ሕይወት የመውረሳችንን ድርሻ የእግዚአብሔር ነው፡፡ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም የሰውን ዘር ሁሉ የማዳንን ድርሻ ለራሱ አድርጓል፡፡ ተንከባክቦናል እስካሁንም ድረስ ይጠነቀቅልናል አንድ ጊዜ ወደ አባቱ ያቀርበንም ዘንድ መለኮታዊ ክብሩን መሥዋዕት አድርጓል፡፡
- እንደዚሁ ባልና ሚስት አንዳቸው ላንዳቸው ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለትዳር አጋራቸውም መሻትና ፍላጎት መሟላት የራሳቸውን ደስታ መሥዋዕት ማድረግ እንዲሁም የትዳር አጋራቸውንም በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም ከሁሉም ይልቅ ደስተኞች እንዲሆኑ ለማድረግ በሙሉ ልብ የተነሳሱ የተዘጋጁም መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የባልና የሚስት ቀዳሚ ኃላፊነት የትዳር አጋራቸው በእግዚአብሔር የሆነ ፍጹም መንፈሳዊ ሕይወትን እንዲመሩ ማብቃት ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ጥልቅ የሆነ ግኑኝነት መመሥረት ወደሚያስችላቸው ደረጃ ለመድረስ እንዲችሉ አንዳቸው አንዳቸውን በማበረታታት ልጆቻቸውም ታላላቅ ክርስቲያኖች ለመሆኑ እንዲበቁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ***የተወደዳችሁ ባሎች!*** ሚስቶች በሕወታቸው በማናቸውም አጋጣሚ በባሎቻቸው መደገፍና በየምክንያቱም የባሎቻቸውን ምክርና እገዛ ማግኘት የሚችሉበት ሁኔታ ሲፈጠርላቸው ፈጽመው እንደሚደሰቱ አስታውሱ!!! ስለዚህ እናንተ ከችግሮች ሸሽታችሁ የራሳችሁን ሕይወት በደስታ እየኖራችሁ ሚስቶቻችሁ ብቻቸውን መከራን እንዲጋፈጡ አትተዋቸው፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 3

## ኃላፊነት

- በቤትም ውስጥ በሚኖረው ሥራ ይህ የእኔ ሳይሆን የሴት ሥራ ነው እያላችሁ ከመተው ይልቅ በሚኖረው ሁሉ ሚስቶቻችሁን አግዙ፡፡
- በቤት ውስጥ ማገልገል ከቤት ውጪ የማገልገልን ያህል ተፈላጊ ነው፡፡ አገልግሎትን እንደምክንያት በመጠቀም ሌላ የምሠራው ታላቅ ሥራ አለ አትበሉ፡፡ በቤት ውስጥ የምንሠራው ሥራ ኖሮ ከተፈለግን ከቤት ውጪ ያለ ማኅበራዊም ሆነ መንፈሳዊ አገልግሎት ለመስጠት ከመውጣታችን በፊት የቤታችንን እንፈጽም፡፡ ‹‹ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፡፡›› *ኤፌ 5፡25፡፡*
- ***የተወደዳችሁ ሚስቶች!*** ወደ ሥራ ገበታችሁ ከመግባታችሁ በፊት በቤታችሁ ያለባችሁን ኃላፊነት መወጣታችሁን በተቻላችሁ መጠን አረጋግጡ፡፡ ባሎቻችሁ ወደቤታቸው ተመልሰው ጥሩ ጣዕም ያለው ምግብና መልካም ድባብ ያለበትን ቤት ማግኘት እንደሚፈልጉ ተረዱ፡፡
- ነገር ግን በቤት ምግብ ከሌለ የቤቱም ሁኔታ የተገላቢጦሽ ከሆነ ባሎች ወደቤታቸው ለመምጣትም ሆነ በቤት ለመቆየት ፍላጎት የሌላቸው ይሆናሉ፤ ይህም መልካም አይደለም!
- እንግዲህ ኃላፊነታችሁን ሁሉ በአግባብ ለመወጣት ያስችላችሁ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ለምኑ! በርግጥም እግዚአብሔር ያስችላችኊልና! ጠቢቡ ሰሎሞንም ‹‹ገና ሌሊት ሳለ ትነሣለች ለቤትዋም ሰዎች ምግባቸውን፥ ለገረዶችዋም ተግባራቸውን ትሰጣለች፡፡›› *ምሳ 31፡15*፣ ‹‹የቤትዋንም ሰዎች አካሄድ በደኅና ትመለከታለች፥ የሀኬትንም እንጀራ አትበላም።›› *ምሳ 31፡27፡፡* በማለት የነገረንም ይህንኑ ነውና፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 3

## የቅድስና ሕይወት

- ‹‹ዳሩ ግን፡፡ እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ፡፡›› ***ቀዳ ጴጥ 1፡16፡፡*** እንደተባለ የእውነተኛ ክርስቲያን ግቡ ቅዱስ መሆን ‹‹የቅድስናን ሕይወት›› መምራት ነው፡፡
- አንዳንድ ሰዎች የቅድስናን ሕይወት መኖር የመነኮሳት፣ የቀሳውስት እና የጳጳሳት ሥራ አድርገው ያስባሉ፡፡ ይህም የተሳሳተ አስተሳሰብ ወይም አመለካከት ነው፡፡
- የቅድስናን ሕይወት መምራት የሰው ልጅ ሁሉ ይልቁንም የባለትዳሮች ሁሉ ግብ ሊሆን ይገባዋል፡፡
- ከሁሉ በፊት ጋብቻ አንድ ወንድና አንዲት ሴትን አንድ የሚያደርግ ምስጢር ነው፡፡ በማስከተልም ‹‹በክርስቶስ የሆነ ጋብቻ›› ተጋቢዎቹን አንድ የሚያደርጋቸው ቅዱስ ጋብቻ ብቻ ሳይሆን ይህ የተቀደሰ ምስጢር ከክርስቶስም ጋር አንድ የሚያደርጋቸው - በርሱ ለመኖርም የሚያበቃቸው ነው፡፡
- ‹‹ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው፡፡›› ***ቀዳ ጢሞ 6፡6፡፡*** እንደተባለው ወንድም ሆነ ሴት የቅድስናን ሕይወት ለመምራት እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወትን ያለማቋረጥ የሚኖሩትና የሚመሩት መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ እግዚአብሔርን መምሰል ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስን ክርስቶስን ለመምሰል የማያቋርጥ ጥረት ማድረግ ነው፡፡
- የትዳር አጋራችንን ስንመርጥ ይህን አስፈላጊ መመዘኛ ትኩረት መስጠትን እንዳንዘነጋ እንመክራለን - እርሱም እግዚአብሔርን ለመምሰል ያለ ዝግጅት ነው፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 3

## የቅድስና ሕይወት

- ይህ ሰው የቅድስናን ሕይወት ለመምራት ያለው ፍላጎት ምን ያህል ነው? ይህ ሰው ወደ (እግዚአነ ኢየሱስ) ጌታችን ኢየሱስ እንዳይቀርብ የሚያደርጉትን ነገሮችን ለመተው ያለው መነሳሳት እንዴት ነው? ይህ ሰው የበለጠ መንፈሳዊ ሕይወት ለመምራት ምን ያህል ጥረት ያደርጋል? የዚህ ሰው የሕይወት ቅደም ተከተሎች ምንድን ናቸው ጌታችን አምላካችንን በሚበልጥ ከፍ ያለ የሕይወት ቅደም ተከተሉ ወይም በዝርዝር ባስቀመጣቸው የሕይወት ውጡኖቹ አናት ላይ ያስቀምጠው ዘንድ ፈቃደኛና ዝግጁ ነውን? ብለን ራሳችንን መጠየቅ ይጠበቅብናል፡፡
- አንዳንድ ጊዜ የእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ተቀባይነት የሌለው ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም የትዳር አጋራችን ሊሆን/ልትሆን የሚችለው/ትችለው ለመለወጥ ዝግጅት ወይም ብቃት ይኑረው ወይም አይኑረው ለማወቅ የሚያስችለንን ጥበብ ለማግኘት ወይም አቅጣጫችንን ለማወቅ ጌታችንን አምላካችንን ኢየሱስ ክርስቶስን መጠየቅ ስለሚያስፈልገን ነው፡፡
- ይህን ማድረግ ከቻልን ይህን ሰው/ሴት በማግባት ወደ ክርስቶስ የምናቀርብበትን ታላቅ ሚና መጫወት እንችላለንና፡፡ ይህ ጉዳይ ማንኛውንም ውሳኔ ከመወሰናችን በፊት ከንስሐ አባታችን ጋር በአግባቡ ልንመክርበት የሚገባ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡
- የገንዘብ ጉዳይን፣ ውበትን፣ የኑሮ ደረጃን ወዘተ የመሳሰሉ አንዳንድ መመዘኛዎችን ወይም ደረጃዎችን ልንተዋቸው እንችላለን፡፡ ነገር ግን ልናገባ የምንመርጠውን አስመልክቶ በመመዘኛ ዝርዝሮቻችን ከላይ ተቀምጦ ሊገኝ የሚገባው ብቸኛውና አንዱ ነገር እግዚአብሔርን መውደድና መፍራት ነው፡፡

# <u>የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 3</u>

## የቅድስና ሕይወት

- ተጋቢዎች ሁሉ ራሳችንን በጋብቻ ለሌላው ለመስጠት ከመወሰናችን በፊት ራሳችንን ለክርስቶስ እግዚአብሔር ልንሰጥ ይገባናል፡፡ እያንዳንዳችን ለክርስቶስ እግዚአብሔር መስጠታችን በጋብቻ ሕይወት ወይም በትዳር ደስታና ዋስትናን የሚያስገኝልን ነው፡፡
- ***የተወደዳችሁ ወንዶች ሆይ!*** የትዳር አጋራችሁን (ሚስት የምትሆናችሁን) ስትመርጡ ‹‹ቁንጅናን›› ወሳኙ መመዘኛ አድርጋችሁ አትቁጠሩ፡፡ ‹‹ውበት ሐሰት ነው፥ ደም ግባትም ከንቱ ነው እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን እርስዋ ትመሰገናለች፡፡›› <u>*ምሳ 31፡30፡፡*</u> እንደተባለ ራስዋን ለባልዋ አሳልፋ የምትሰጥ የባልዋንም ሕይወት በክርስቶስ ሰላምና ደስታ መሙላት የሚቻላት ሚስት እግዚአብሔርን መምሰልን ምርጫዋ ያደረገች ሚስት ብቻ ናት!!!
- ***የተወደዳችሁ ልጃገረዶች ሆይ!*** ባለጠጋ ወንድ ማግኘት ከሁሉ በላይ ትርፍ እንደሆነ እንዳታስቡ፡፡ ይህ ወንድ አንቺን ትቶ ወደ ሌላይቱ ሴት የሚሄድ ብሎም ባንቺ ላይ የሚዋሽ ከሆነ የገንዘቡ ጥቅም ምንድር ነው? ዘወትር በማንኛውም ሰዓት ባልሽን መመልከት የምትችይ አድርገሽ ታስቢያለሽ? እንደዚህ ካሰብሽ በርግጥም ታላቅ ስህተት ተሳስተሻል ማለት ነው፡፡
- በርግጥም እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ ትእዛዙን የሚጠብቅ በርሱ የሚታመን ባል ብቻ ፍጹም ታማኝና አፍቃሪም ነው፡፡ ከተጫጫችሁበትም ጊዜ አንስቶ የምትከታተሉት መንፈሳዊ መርሐ ግብር ይኑራችሁ፡ ስለዚህ ከመጋባት በፊት ጌታችን ክርስቶስን በመካከላችሁ ለማድረግ ፈቃደኝነቱ ያላችሁ ሁኑ፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 3

## የቅድስና ሕይወት

### ከዚህ በታች የምንመለከታቸው ባልና ሚስት በጋራ ልንፈጽማቸው የሚገቡ ተግባሮች ናቸው

1. **ጸሎት**

- የዘወትር ጸሎታችንን ለመጸለይ ጊዜን የመመደብን አስፈላጊነት ማመን፡፡ጊዜው አጭር ቢሆንም ለጸሎት በእግዚአብሔር ፊት መቆማችን ጌታችንን በመካከላችን እንዲገኝ ከማድረጉም በላይ በመካከላችን ያለውን ግኑኝነት የበለየ የጠበቀ ያደርገዋል፤ በርሱም የተዋሐድን እንሆናለን፡፡

2. **መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና ማጥናት**

- ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ልናነብ በሚገባን ክፍል ላይ እንወስን፣ ባነበብነውም ላይ የቤተክርስቲያንን ትውፊትና ትርጓሜያት መሠረት አድርገን እንነጋገር፡፡

3. **ጾም**

- ጌታችን እንዳስተማረን በቤተ ክርስቲያን በተወሰነልንም ሆነ እኛም ጨምረን በምንጾመው የግል ጾም አብረን እንጹም፡፡ በጾማችንም ጊዜ ጌታችን በነገር ሁሉ ይመራን ዘንድ መጸለያችንም ከሁሉ በላይ እናደርገው ዘንድ የምንመከረው መንፈሳዊ ትሩፋት ነው፡፡

4. **የንስሐ አባት**

- ሳያቋርጡ በንስሐ ሕይወት መኖር እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወትን የመምራት የማዕዘን ደንጊያ ነው፡፡ ዘወትር ራሳችንን የመመርመርን፣ ኃጢአትን የመናዘዝንና ንስሐ የመግባትን ልምድ እናዳብር፤ ለዚህም አንድ የተወሰነ የንስሐ አባት ይኑረን፡፡

# <u>የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 3</u>

## የቅድስና ሕይወት

**ከዚህ በታች የምንመለከታቸው ባልና ሚስት በጋራ ልንፈጽማቸው የሚገቡ ተግባሮችን ነው**

5. **ቅዳሴ ማስቀደስ ቅዱስ ቁርባን መቀበል**

- ‹‹*ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ*፡፡›› ***<u>ዮሐ 6፡56፡፡</u>*** ቢያንስ ከጋብቻችን ቀን ጊዜ ጀምሮ በሳምንት አንድ ቀን ማስቀደስና ቅዱስ ቁርባን መቀበላችንን እርግጠኞች እንሁን፡፡

6. ***መንፈሳዊ ጉባኤያትን መሳተፍና አገልግሎት መስጠት***

- ግኑኝነታችንን የበለጠ ሊያጠናክር በሚችል አገልግሎትና መንፈሳዊ ጉባኤያትን በመሳተፍ የጋራ ፈቃደኝነቱ ያለን እንሁን፡፡

7. **‹‹*አሥራት*›› መክፈል**

- ‹‹ይህንም እላለሁ፡፡ በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል፥ በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል፡፡›› ***<u>ካል ቆሮ 9፡6፡፡</u>*** እንደተባለ ከምናገኘው አሥራታችንን ማውጣታችን ሕይወታችን በርሱ የተባረከ እንዲሆን ስጦታውንና ባለጠግነቱንም አብዝተን እንድንቀበል ያበቃናል፡፡
- እነዚህ የመንፈሳዊ ሕይወት አጥሮች ማንኛውም ክፉ ነገር ወደ ትዳራችን እንዳይገባ የሚከላከሉ ናቸው፡፡ የተለመደም ሆነ ያልተለመደ የሕይወት ፈተናዎች ስንጋፈጥ ከማንኛውም ጉዳት የተጠበቅን ሆነን ወደ ክርስቶስ እግዚአብሔርበመቅረባችን እንደሁም ውጊያችንን ሁሉ በመዋጋት ፍጹም ሰላምንና ደስታን እንደሚሰጠን በማመናችን ፈተናውንና የዲያቢሎስን ወጥመድ ሁሉ ድል እናደርጋለን፡፡

# ይቆየን፡፡

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org